ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
Solidarity Movement for a New Ethiopia

## በዑጋንዳ የተጨፈጨፉትን ወገኖቻችንን እናስብ!

ብዙዎቻችን እንደተከታተልነው በቅርቡ በዑጋንዳ ካምፓላ በራግቢ ክለብና የኢትዮጵያ መንደር በተባለ ምግብ ቤት የተጠመዱ ቦንቦች በደረሰው ጭፍጨፋና ዕልቂት ምክንያት የ 74 ሰዎች ዉድ ህይወት ሲያለፍ ከ70 በላይ የሚሆኑ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ከጥቃቱ ሰለባዎች መካከል ኢትዮጵያውያን ፣ ኤርትራዊያን ፣ ዑጋንዳውያን ፣ ህንዳውያን እና የሌሎች አገር ዜጎች እንደሚገኙበት የታወቀ ሲሆን እስካሁን ማንነታቸው ያልታወቁ ሟቾች እና በአካላቸው ላይ በደረሰው ከፍተኛ አደጋ ማንነታቸውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆኑት ቁጥርም በርካታ ነው፡፡

ለኛ የዚህ አሰቃቂ አደጋ ሰለባዎች ኢትዮጵያውያን ወይም ኤርትራዊ ብለን በቁጥር ከመጥቀስ ያለፈ ስም፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ቤተሰብ ወዘተ ያላቸው ወንድሞችና እህቶቻችን ናቸው፡፡ ቁጭታችንና ሃዘናችን ከዘር እና ከድንበር ያለፈ ነው፡፡ የቤተሰቦቻቸው ሃዘን የእኛም በመሆኑ የሟች ቤተሰቦቸ መጽናናትን እንዲያገኙ የቆሰሉትንም በቶሎ አገግመው ጤናቸው እንዲስተካከል ጸሎታችን ነው፡፡




እኛ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ውስጥ የምንገኝ፤ ይህ ዘግናኝ እልቂት የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን በጸሎታቸው እንዲያስቡ እና በሚችሉት ዓቅም ሁሉ በገንዘብ እንዲረዱ ለኢትዮጵያውያን እና ለኤርትራዊያን ወዳጆቻችን በሙሉ ጥሪ ልናደርግ እንወዳለን፡፡ ከዚህ አኳያ አብያተክርስቲናት፣ መስጊዶች እንዲሁም ሌሎች ወገኖች በዚህ የገንዘብ ማሰባሰብ ተግባር ላይ ቀዳሚ ቢሆኑና የሚሰበሰበውንም ለተጎጂ ቤተሰቦች፣ ለቀብር ሥርዓት እንዲሁም ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ላላቸው ሌሎች ጉዳዮች ባፋጣኝ እንዲውል ቢያደርጉ የብዙዎችን ሸክም ሊያቃልሉ ይችላሉ፡፡

እስካሁን በደረሰን መረጃ መሠረት የንቅናቄያችን ንቁ አባልና ተሳታፊ የሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ ከሟቾች መካከል እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል፡፡ ይህ ወገናችን እንደሌሎቹ ሁሉ የአቶ መለስ አፋኝና ኢዲሞክራሲያዊ አስተዳደር አንገፍግፎት አገሩን ጥሎ በስደት በካምፓላ የሚገኝ ነበር፡፡ ለዚህ ወንድማችን ሞት ተጠያቂ ድርጊቱን በቀጥታ የፈጸሙት ብቻ ሳይሆኑ በተወለደበት አገር በነጻነት እንዳይኖር ከአገሩ እንዲሰደድ ያደረገው የመለስ አገዛዝም ጭምር ነው፡፡ ይህ አገዛዝ ሱማሌ ወገኖቻችንን በማግለል ለከፋ ዕልቂት እና ስቃይ እንዲዳረጉ በፈጸመው ተግባር በጦር ወንጀለኝነት ተጠያቂ ነው፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን የዚህ አገዛዝ ሰለባ በመሆናቸው አገራቸውን ጥለው በሚሰደዱበት ወቅት አብዛኛዎቹ በሊቢያ ፣ በግብጽ ፣ በታንዛኒያ ፣ በጃፓን ፣ በሶሪያ ወዘተ አገሮች እስርቤቶች እየማቀቁ ሲሆን ሴቶች እህቶቻችንም ለወሲብ ንግድ ተጋልጠዉ በተለያዩ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ፍዳቸውን እያዩ ይገኛሉ፡፡ በቀይ ባሕር በመስጠም ፣ በስደት፡ በረሃብና በበሽታ በደቡብ ሱዳንና በዑጋንዳ እንዲሁም በኬንያ መከራቸውን እያዩ ያሉትን ወገኖቻችንን ቆጥረን የምንዘልቀው አይደለም፡፡

ታዲያ ይህ ሁሉ ሲሆን ‹‹አምላክ ሆይ መቼነው ይህ መከራና ስቃይ የሚያበቃው?›› ብለን የምንጠይቅ ጥቂቶች አይደለንም፡፡ እነዚህ ወገኖቻችን ከሚደርስባቸው ስቃይ ለማምለጥ ዉድ ሃገራቸዉን ጥለው ቢሸሹም ለሌሎች ዕኩይ ተግባር ሰለባ እንዲሆኑ ተዳርገዋል። በአገራቸው በነጻነት እንዳይኖሩ ያደረጋቸው ይኸው በመለስ

የሚመራው የህወሃት ጨቋኝ አገዛዝ ሲሆን አገዛዙ በማናለብኝነት በኢትዮጵያውን ላይ እያደረሰ ካለዉ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ዉስጥ ግድያ ፣ የግዳጅ ወሲብ ፣ ዘረፋ ፣ እስርና አፈና የሚጠቀሱ ናቸዉ። በጋምቤላ በአኙዋክ ሕዝብ ላይ የደረሰው ዕልቂትና የዘር ማጥፋት ወንጀል ፣ በኦጋዴን ክልል በኢትዮጵያ ሶማሌዎች ላይ፣ እንዲሁም በጸረአሸባሪነት ዘመቻ ሰበብ በሶማሊያውያን ላይ የፈጸመው ግፍ በጦር ወንጀለኝነት የሚያስጠይቀው ጥቂቶቹ ተግባሮቹ ናቸው፡፡

እኛ የንቅናቄው (**SMNE**) አባላት ይህንን የሰብዓዊ መብት ጥሰት አጥብቀን የምንቃወም መሆናችንን በተደጋጋሚ የገለጽን ሲሆን ሊጋሽ አገራትንም መለስ እንደሚለው ሳይሆን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አገዛዝ በመልካም አስተዳደር መቀየሩ ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም ወሳኝነት ያለው መሆኑን በተደጋጋሚ ስናሳስብ ቆይተናል፡፡ ሆኖም ግን የዓለም መንግሥታት ለዚህ ማስጠንቀቂያ ጆሮ ዳባ የሰጡ ሲሆን ይኸው ዝምታቸውም የቀጣናው ሰላም እጅግ አደጋ ላይ እንዲወድቅ ያደረገው ብቻ ሳይሆን አክራሪ አመለካከት ያላቸው እንደ አልሸባብ ያሉ ጽንፈኛ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ በማድረጉ አሁን በካምፓላ እንዳየነው ዓይነት እልቂት እንዲደርስ ምክንያት እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ ለእንዲህ ዓይነቱ ተግባር ኃላፊነቱን የሚወስዱት በክልሉ የሚገኙት አምባገነናዊ መንግሥታት ብቻ ሳይሆኑ የእነርሱ ደጋፊ እና ደጓሚ የሆኑት ምዕራባዊንም ጭምር እንደሆኑ በድጋሚ ማስገንዘብ እንወዳለን። እነዚሁ ምዕራባዊን ናቸው እንደ መለስ ያለውን አምባገነን «የጸረ አሸባሪነት ዘመቻ አጋር» በሚል ሽፋን በገንዘብ እየረዱ አካባቢውን ለእንዲህ ዓይነት ቀውስ የዳረጉት፡፡

የቀድሞው የሶማሊያ ጠ/ሚ/ር የነበሩት ዶ/ር አሊ ካሊፍ ጋሊድ በቅርቡ ይህንን ጉዳይ አስመልክተው እንደተናገሩት፤ በሶማሊያ ፈጣንና ውጤታማ ለውጥ እንዲመጣ ከተፈለገ በዖጋዴን አካባቢ ያለው ችግር በመጀመሪያ መፈታት አለበት፤ የዖጋዴን ችግር እንዲፈታ ደግሞ አዲስ አበባ ላይ መልካም አስተዳደር ሊመሰረት ግድ ሲሆን ይህም በኢትዮጵያ የሚመሠረተው መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችል አሳስበው ነበር፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ሕዝባዊ መንግሥት በኢትዮጵያ እንዲመሠረት ለእውነት ፣ ለፍትሕ ፣ ለእኩልነት የሚቆሙ ቅን መሪዎች በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ምስራቅ አፍሪካ ያስፈልጉናል፡፡ እኛ በአፍሪካ ቀንድ የምንኖር መጻዒ እድላችንን ብሩሕ ማድረግ የምንችል በመሆኑ ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ራሳችንን በማነሳሳት ለልጆቻችን የተሻለ ተስፋ ልናመጣላቸው መጣር አለብን፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ መተባበርና መደጋገፍ ይኖርብናል፡፡ ለዚህም ፈጣሪ ይርዳን፡፡

በዑጋንዳ ካምፓላ የሞቱን ወገኖቻችን የተሻለ እንድንሰራና እንድንተባበር ምክንያት እንዲሆኑን የሁላችንም ምኞት ነው፡፡ አመለካከታችንን አስፍተን የእያንዳንዳችን ነጻነት በሁሉም ነጻነት ላይ የተመረኮዘ መሆኑን በማመን እንዲሁም ከዘርና ከጎሣ ክልል አልፈን ለሰብዓዊነት በማሰብ ለአገራችን የተሻለውን ለማድረግ ሁላችንም በኅብረት እንነሳ፡፡

አምላካችን የሟቾችን ነፍስ ይማርልን፤ በአካል ለተጎዱት ምህረትና ፅናትን፤ ላዘኑት ቤተሰቦች መጽናናትን ይስጥልን፡፡

አባንግ ሜቶ
ዋና ዳይሬክተር
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
***********************************************************************************************
*************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*